# «የመድረክ አመራሮች በራሳቸው የማይተማመኑና ህዝባዊ ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው»

ኢ/ር ኃይሉ ሻውል እና አቶ ማሙሸት አማረ

## መኢአድ በጠራው ስብሰባ ከ800 በላይ ሰው ተገኘ

መኢአድ ባለፈው እሁድ በውሃ ልማት ጽ/ቤት አዳራሽ ባደረገው ህዝባዊ ስብሰባ ከ800 በላይ ሰው ተገኝቶ ነበር፡፡ ስብሰባውን የተከታተለው የኢትዮ-ቻናል ሪፖርተር እንደዘገበው መድረኩን የመሩት ኢ/ር ኃይሉ ሻውልና ሌሎች የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ናቸው፡፡ አቶ ማሙሸት አማረ፣ አቶ ሳምሶን ጌታቸው፣ አቶ ብዙአየን ገ/ማርያም፣ ኮ/ል ትርሲት ገ/መስቀልና አቶ አክሊሉ የኔነህ በወቅቱ ከኢ/ር ኃይሉ ጎን መድረኩ ላይ እንደነበሩም ዘጋቢያችን አስረድቷል፡፡

ኢ/ር ኃይሉ እና አቶ ማሙሸት አማረ በንባብና በማብራሪያ መልክ ባቀረቡት የምርጫ ቅስቀሳ ፓርቲያቸው «የኢህአዴግ ተለጣፊ ነው» በሚል የተከፈተበትን የስም ማጥፋት ዘመቻ በተደጋጋሚ አምርረው መቃወማቸውን ዘጋቢያችን ጠቅሶ በተለይም የመድረክ አመራሮችን አጥብቀው መተቸታቸውን ገልፆልናል፡፡

እነዚህ ሁለት የመኢአድ አመራሮች ስለ ፓርቲያቸው ሲያስረዱ መኢአድ በሰላማዊ ትግል የሚያምን፣ መሆኑንና ኢትዮጵያ እንዳትገነጣጠል አንቀጽ 39ኝ የመሬትን የመንግስት ይዞታነትና የባህር በር ማጣትን ሲቃወም መቆየቱን እንዳብራሩ ዘጋቢያችን ተናግሯል፡፡ «የኤርትራን መገንጠል ፕ/ር አስራት በወቅቱ የተቃወሙ ቢሆንም፣ በዛን ወቅት አገር ካስገነጠሉት ውስጥ ዋናዎቹ የዛሬ የመድረክ ፓርቲ አመራሮች ነበሩበት» ብለዋል የመኢአድ አመራሮቹ፡፡

እነዚህንም ሲዘረዝሩ፡-

1ኛ. አቶ ስዬ አብርሃ የመከላከያ ሚኒስቴር የነበሩ

2ኛ. አቶ ገብሩ አስራት የትግራይ ክልል ፕሬዘዳንት የነበሩ

3ኛ. ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የአገሪቱ ፕሬዘዳንትና በወቅቱ ማስታወቂያ ሚኒስትር የነበሩ

4ኛ. ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ምክትል የትምህርት ሚኒስቴር የነበሩ

5ኛ. ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከአሜሪካ የክብር እንግዳ ሆነው ተጋብዘው የድራማው ተዋናይ የነበሩ በማለት አቅርበዋቸዋል፡፡

ኢ/ር ኃይሉ ሻውልና አቶ ማሙሸት አማረ በስብሰባው በሰጡት ማብራሪያ «አቶ ስዬ አብርሃ መኢአድ ተለጣፊ ነው በማለት የለመዱት ውሸት አልለቅ ብሏቸው ይቀባዥራሉ» ብለዋል፡፡ ስለኢ/ር ግዛቸው ሁለቱ የመኢአድ አመራሮች ሲናገሩ ደግሞ «የኢህአዴግ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክትል ኮሚሽነር የነበሩት ግለሰብ ወደ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት እንዴት ሊገቡ ቻሉ? የሚለውን ማየት ያስፈልጋል» ማለታቸውን ሪፖርታችን አስረድቷል፡፡ አመራሮቹ ቀጠል አድርገውም «ኢ/ር ግዛቸው በመጀመሪያ የኢዴፓ አባልና ስራ አስፈፃሚ፣ ከዚያም የመኢአድ አባልና ስራ አስፈፃሚ፣ ቀጥሎም የቅንጅት አባልና ስራ አስፈፃሚ የሆኑና ቅንጅትን በማፍረስም ቀዳሚ ናቸው፡፡ ታዲያ እኚህ ሰው በዩኒቨርሲቲ መምህርነት እንዴት ሊቀጥሉ ቻሉ? ኢህአዴግስ እንዴት

ለእሳቸው ሩህሩህ አንጀት አገኝ?» ሲሉ መጠየቃቸውን የሪፖርተራችን ዘገባ ያመለክታል፡፡

ስብሰባውን የተከታተለው ሪፖርተራችን ኢ/ር ኃይሉና አቶ ማሙሸት በተለይም በኢ/ር ግዛቸው ላይ ያላቸው ጥላቻ የመረረ መሆኑን ለመረዳት እንደቻለ ይናገራል፡፡ ሁለቱ አመራሮች በየተራ ባደረጉት ገለፃ «ኢ/ር ግዛቸው ከአንድ ፓርቲ ወደ ሌላ የመገለባበጥ ችሎታ ያላቸውና በቆሙበት የማይረጉ ፖለቲከኛ ናቸው» ካሉ በኋላ መድረክ ውስጥ ለምን እንደገቡም አብራርተዋል፡፡ በዚህ ማብራሪያቸው «ትላንት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክትል ኮሚሽነር በነበሩበት ወቅት ህዝቡን ማማከር እንደነውር የሚቆጥረው አዕምሯቸው ሳይለወጥ ዛሬ የአንድነት አመራሮችን ፈቃድና ይሁንታ ሳያገኙ ህብረ ብሔራዊ የሆነ ድርጅታቸውን በብሔር ከተመሰረተና ከግለሰቦች ጋር አጣመርኩት ይላሉ» በማለት መናገራቸውን ሪፖርተራችን አስረድቷል፡፡ «ኢ/ር ግዛቸው መኢአድ ተለጣፊ ነው እያሉ በየመንደሩ ያወራሉ» ያሉት የመኢአድ አመራሮች በፓርቲያቸው አባላትና አመራሮች ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሟቸው እያለ ምንም ያልመሰላቸው «አፍራሽ ተልዕኮ ስላላቸው ያንን እየተወጡ በመሆኑ ነው» ሲሉም እንደገለፁ ሪፖርተራችን ጠቁሟል፡፡

ኢ/ር ኃይሉና አቶ ማሙሸት በመቀጠል ወቀሳ ያቀረቡባቸው ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ናቸው፡፡ እንደ ሪፖርተራችን ዘገባ ሁለቱ አመራሮች «ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ገና ከጠዋቱ ኢህአዴግን የተቀላቀሉት እኮ ምክትል የትምህርት ሚ/ር በነበሩበት ጊዜ ነው፡፡ እኚህ ግለሰብ በእያንዳንዱ የፖለቲካ ጥምረት፣ ህብረትና ውህደት ውስጥ በሊቀመንበርነት ያልተሳተፉበት የፖለቲካ ድርጅት የለም፡፡ ከኢህአዴግ እስከ ተቃዋሚነት ማፍረስ እንጂ መገንባት በእሳቸው ከቶ አይታወቅም» ሲሉ በሰፊው ተናግረዋል፡፡

ፕ/ር በየነ የደቡብ ህዝቦች ህብረትን፣ የአማራጭ ኃይሎች ህብረትንና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረትን መርተው ፓርቲዎቹ መፍረሳቸውን የመኢአድ አመራሮች እንደ ምሳሌ ጠቅሰው «ታዲያ ተለጣፊው ማነው?» ሲሉም ለህዝቡ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

«መኢአድ እያራመደ ያለው ሰላማዊ ትግል ነው» በማለት የተናገሩት የመኢአድ አመራሮች ስለምርጫ ስነ-ምግባር ድርድሩ ሂደትም በአካሄዱት ህዝባዊ ስብሰባ አብራርተዋል፡፡ በማብራሪያቸው «ትልቁ የመፍትሄ ቁልፍ መወያየትና መደራደር ነው፡፡ መኢአድ ይሄንኑ የሰላማዊ ትግል መፍትሄ የሆነውን ድርድር በማድረግ የሀገርንና የህዝብን ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል ትልቅ ስራ ሰርቷል፡፡

በዚያ ድርድር የፓርቲያችን አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር፡፡ ለህዝባችንና ለአገራችን ጥቅም ቅድሚያ በመስጠትና የመኢአድን ህልውና ለማስጠበቅ ትልቅ ስራ በመስራታችንና በስነ-ምግባር ደንቡ በመሳተፋችን አያሌ ጥቅም አግኝተናል» ማለታቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል፡፡

የመድረክ አመራሮች ከኢህአዴግ ጋር ለብቻ ለመደራደር የጠየቁት ለምን እንደሆነ ግራ እንደገባቸው ኢ/ር ኃይሉ ጠቅሰው ቢሆንም መአኢድ በድርድሩ በመካፈሉ ባገኙት አጋጣሚ ተለጣፊ ነው እያሉ የፓርቲውን ስም ጥላሸት ለመቀባት ሲውተረተሩ መታየታቸውን አስረድተዋል፡፡ በ2002 ምርጫ ዕጩ የማስመዝገቢያ ቀን ባለፈበት ወቅት መኢአድ «ዕጩዎች ካለ አግባብ እንዲወጡብን ተደርጓል» ብሎ በድርድሩ መሰረት

በመጠየቁና ምርጫ ቦርድም ፈቃደኝነት በማሳየቱ ቀኑ ሲራዘም የመጀመሪያው ተጠቃሚ መድረክ ሊሆን መቻሉንም ኢ/ር ኃይሉ አውስተዋል፡፡

ሁለቱ የመኢአድ አመራሮች ለፓርቲያቸው አባላትና ደጋፊዎች ባደረጉት ንግግር መድረክ አንድም ቀን ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ እንድትፈታ በቃልም ሆነ በደብዳቤ አለመጠየቁን ገልፀው «መኢአድ ይሄን ጥያቄ በማቅረቡ በምን መለኪያ ተለጣፊ ያስብለዋል?» ሲሉም አስረድተዋል፡፡

ኢ/ር ኃይሉ ሻውልና አቶ ማሙሸት አማረ በገለፃቸው በእያንዳንዱ የመድረክ ዕጩ ተወዳዳሪ ፖስተር ስር የወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ የሀዘን ፎቶ እንዲለጠፍ መደረጉን በተመለከተም «መድረክ በራሱ የሚተማመን አመራር የሌለውና በህዝብ የማይተማመን መሆኑን ያሳያል፡፡» ብለዋል፡፡ «የወ/ሪት ብርቱካንን ፎቶ መለጠፍ የማንን አንጀት ለመብላት ይሆን?» ያሉት የመኢአድ አመራሮች የሚበጀው ማስመሰል ሳይሆን ሆኖ መገኘት መሆኑንም በውሃ ልማት አዳራሽ ለተገኘው ተሰብሳቢ አስታውቀዋል፡፡

ይሄ በእንዲህ እንዳለ በተለያየ የኃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ የመኢአድ አባላት አመራሩ ህገ ወጥ አካሄድ ላይ ነው» ሲሉ ለኢትዮ-ቻናል በሰጡት መግለጫ ገልፀዋል፡፡ በተለይም የፓርቲው ዋና ፀሐፊ ተብለው የተሾሙት አቶ ማሙሸት አማረ በየሣምንቱ በሚደረገው የፓርቲው አባላት የፖለቲካ ትምህርት መግለጫ ሲሰጡ እያንዳንዱ አባል መድረክ በሚያከናውነው ማንኛውም ህዝባዊ ስብሰባ ተገኝቶ ጥያቄ በማንሳት እንዲያወግዘው መመሪያ መስጠታቸውን በመግለጫቸው አስታውቀዋል፡፡ በመኢአድ ውስጥ የአንድ መንደር ስብስብ እየተበራከተ መምጣቱን በመግለጫቸው ጠቅሰውም እንደ ምሳሌ በአዲስ አበባ ፓርቲው በዕጩነት ያቀረባቸውን ግለሰቦች ዘርዝረዋል፡፡

በወረዳ 23 ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል (ሰሜን ሸዋ)፣ በወረዳ 19 ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ (ሰሜን ሸዋ)፣ በወረዳ 17 አቶ ማሙሸት አማረ (ሰሜን ሸዋ)፣ በወረዳ 18 ኮ/ል ትርሲት ገ/መስቀል (ሰሜን ሸዋ)፣ በወረዳ 2 አቶ ደርሰህ አበራ (ሰሜን ሸዋ)፣ በወረዳ 11 አቶ መሀተመሥላሴ (ሰሜን ሸዋ)፣ እንዲሁም በወረዳ 16 አቶ አሰፋ ሀብተወልድ (ሰሜን ሸዋ) መሆናቸውን መግለጫው አመልክቶ «እነዚህ በመኢአድ ስም እያታለሉን ያሉ የአንድ አካባቢ ስብስቦች ናቸው» ብሏል፡፡

በመግለጫው ስማቸው የሰፈረ የመኢአድ አባላት

1. ጌታነህ ዓለም (አደራጅና የሰሜን ቀጠና አስተባባሪ)
2. አሸናፊ አስናቀው (የቦሌ ክ/ከተማ ዋና ፀሐፊ)
3. ከበደ ታዬ (አደራጅና የምዕራብ ቀጠና አስተባባሪ)
4. አሸናፊ ግርማ (የአዲስ አበባ ወጣቶች ም/ቤት ስራ አስፈፃሚ የማህበራዊ ዘርፍ ኃላፊ)
5. አሸናፊ አንተነህ (የአዲስ አበባ ወጣቶች ም/ቤት ስራ አስፈፃሚ) የቦሌ ክፍለ ከተማ ወጣቶች ሰብሳቢ
6. ታዬ መዝገበ (የአዲስ አበባ ወጣቶች ም/ቤት ስራ አስፈፃሚና የጥናትና ምርምር ዘርፍ ኃላፊ)
7. ቸርነት እሸቱ (የአዲስ አበባ ወጣቶች ም/ቤት ስራ አስፈፃሚና የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወጣቶች ሰብሳቢ)
8. ኃ/ገብርኤል ታምራት (የአዲስ አበባ ወጣቶች ም/ቤት ዋና ሰብሳቢ) ናቸው፡፡